የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፴፮
አዲስ አበባ ሀምሌ ፯ ቀን ፪ሺ፲፫

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

27th Year No 36
ADDIS ABABA 14th July, 2021

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፶፯/፪ሺ፲፫

ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ፋይናንስ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ……..ገጽ ፲፫ሺ፬፻፷፮

## Content

Proclamation No 1257/2021

International Development Association Additional Financing Agreement for Small and Medium Enterprise Finance Project Ratification Proclamation..……………………….Page 13466

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፶፯/፪ሺ፲፫

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ፋይናንስ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል አንድ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር. (፩፻፴፱ ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር) ተጨማሪ ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ሚያዚያ ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም በአካሄደው ፭ኛ ልዩ ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

## PROCLAMATION NO. 1257/2021

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS**, the Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association shall provide to the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount equivalent to One Hundred Thirty Nine Million Special Drawing Rights (SDR 139,000,000.00) additional financing for Small and Medium Enterprise Finance Project, was signed in Addis Ababa on 23rd day of April, 2021;

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its 5th special session held on 7th day of July, 2021;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ “ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ፋይናንስ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ከዓለም አቀፉ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፶፯/፪ሺ፲፫” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ሚያዚያ ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 6864-ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን አንድ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር. (፩፻፴፱ ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሀምሌ ፯ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**NOW, THERFORE**, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Federal Democratic Republic of Ethiopian Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the “International Development Association Additional Financing Agreement for Small and Medium Enterprise Finance Project Ratification Proclamation No. 1257/2021”.

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement Number 6864-ET signed in Addis Ababa on 23rd day of April, 2021 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan an amount equivalent to One Hundred Thirty Nine Million Special Drawing Rights (SDR 139,000,000.00) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force up on its publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa, on this 14th Day of July, 2021**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRAT REPUBLIC OF ETHIOPIA**